የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.46
ADDIS ABABA 14th June, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ…………ገጽ ፱ሺ፮፻፷፫

## Content

Proclamation No.1014./2017

Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti for theDevelopment, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network Ratification Proclamation ………………………. --Page 9663

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የሁለትዮሽ ስምምነት በአዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሰት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### Proclamation No. 1014/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE BILATERAL AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF DJIBOUTI FOR THE DEVELOPMENT, OPERATION, AND MANAGEMENT OF STANDARD GAUGE RAILWAY NETWORK**

**WHEREAS,** the Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network was signed in Addis Ababa on the 14th day of July 2012;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 25th day of May, 2017;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ ‹‹በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲፬/፪ሺ፱›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉ የሁለትዮሽ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈፃሚ አካላት</u>**

ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስአበባ ሰኔ ፯ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network Ratification Proclamation No.**1014./2017**’’

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network, signed on the 14th day of July, 2012 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organs</u>**

The Ministry of Transport of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa on this 14th day of June, 2017.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**